## የለውጥ ፍላጎትና ንፋስ በኢትዮጵያዊ ወይስ በግብጽ መንፈስ

ከሙሼ ሰሙ

ከሎሚ መጽሔት

እድሜ እንደ አለመታደል ሆኖ በበርካታ ሰዎች ግምገማን እንደበጎ የለውጥ መሳርያ አይዩትም፡፡ በእኔ እምነት እድልና ሁኔታ በፈቀደ መጠን በሰከነ ልቦና ቆም እያሉ አካባቢንና ዙርያ ገባውን መገምገም ራስን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ለመናበብ ጠቃሚ መሳርያ መሆኑን መቀበል የግድ ያላል፡፡ ጠንካራ ጎንን ይበልጥ ለማጠንከርና ደካማ ጎንን ለማረም ግምገማ እድል ይፈጥራል፡፡ ግምገማ በአጠቃላይ የወደፊት ጎዞን ለማሳመር ወሳኝ ምዕራፍ ነው። በተለምዶ ብዙዎቻችን የጊዜ እጥረትንና በስራ መጠመድን መንስኤ በማድረግ እራሳችንና አካባቢያችንን የመገምገም ልምድ የለንም። ቆም ብለን ወደ ኃላ ለመመልከት መስከረም መጥባቱን እንሻለን፡፡ በአብዛኛው መስከረም ጥቅምትን ፣ ጥቅምት ሕዳርን እያቀበለን መንጎዳቸው ተፈጥሯዊ መሆኑንን እንዘነጋለን፡፡ ሌላ መስከረም ካልመጣ በስተቀር ዘመን ቢቆጠርም የለውጥ ሽታ የማይሸተን ለዚሁ እንደሆነ እገምታለሁ። የብዙዎቻችን ስጋት ጥርጣሬ፣ ተስፍችንና ሕልማችን መስከረም ላይ ተቀስቅሶ እዛው ወር ላይ ይደመደማል፡፡ በዚህም ምክንያት እንደ ባሕል የያዝነውና አምና ያገለገለ መሳሪያ፤ ለዘንድሮም ያገለግላል የሚለው ብሒላችን አብዛኛውን ጊዜ እውነት ሊሆን ቢችልም ሁልጊዜ ግን እውነት ሊሆን እንደማይችል ለመረዳት ስጋዊም ሆነ መንፈስ ዝግጁነት ያስፈልገናል የሚል እምነት አለኝ።

ያለፈውን አንድ ዓመት መገምገም ቀላል ጉዳይ አይደለም። በተለይ ደግሞ ሃገራችን ኢትዮጵያ በፈርጀ ብዙና ውስብስብ ችግሮች ተወጥራ የተያዘች እንደመሆኖ መጠን ለመጽሔት በሚመጥን ደረጃ ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውንና ማህበራዊ ጉዳዮችን መፈተሽ ፈታኝ ነው። ብዙ ሊባልበት እየተገባ ብዙ ሊረሳ ይችላል፡፡ በአሁኑ ወቅት ድህነቱ፣ ስራ አጥነቱ፣ የሰብአዊ መብት ረገጣውና የመልካም አስተዳደር እጦቱ የሚያንገሸግሽ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እሙን ነው፡፡ ብልጭ ብለው የነበሩ በርካታ ተስፋ ሰጭ ጭላንጭሎች በኢህአዴግ በኩል ቁርጠኝነቱ፣ አሳታፊነቱና ሕዝባዊነቱ እየሟሸሹ በመሄዱ "ጭላጭሎቹ" ገድል ሆነው በትረካ ዓለም ውስጥ ብቻ ቀርተዋል፡፡ ዛሬ ላይ ከሃያ አንድ ዓመት ጉዞ በኃላ የቀረን ነገር ቢኖር "ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶችን" ለማስፈን አቅደን ነበር የሚለው የኢህአዴግ ውዳሴ ከንቱ ብቻ በመሆኑ የዛሬና የነገ እጣ ፈንታችን ምን ላይ እንደሚገኝ መገመት እንኳን አዳጋች ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ነጮቹ እንደሚሉት ሃያ አራት ሰባት (Twenty four seven) ከኢህአዴግ መገናኛ ብዙሃን የሚዘንበውንና በካድሬዎቹና በአንድ ለአምስት ሰራዊቱ በር ለበር ከሚዥጎደጉዱት ፕሮፓጋናዳዎች መሃል እውነታውን ፈልቅቆ ማውጣት ቢያንስ ለብዙሃኑ ዜጋ ከባድ ፈተና ነው። ለበርካታ ዓመታት ፖለቲካችን የራሱ እግርና እውነትን ምርኩዝ አድርጎ እንዳይቆም ቀስፎ የያዘው ዋነኛ በሽታ ይህው ትንፍሽ የሚያሳጥረው የኢህአዴግ ካድሬዎች የፕሮፓጋንዳ ውርጅብኝ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

ዛሬም እንደ አምናውና ካቻምናው ሁላ ኢትዮጵያና ልጆቿ በከፍተኛ የለውጥ ጥያቄ ውስጥ እየተናጥን እንገኛለን። የለውጥ ፍላጎታችን እንደ ችግራችን መሰረተ ሰፊና ፈርጀ ብዙ ነው። ዛሬን ለማደር ሲባል ከምንተናነቀው የዳቦ ጥያቄ አንስቶ ውስብስብ እስከሆነው የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ድረስ የዘለቁ ጥልቅና በርካታ ጥያቄች አሉን። ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ በተለይ ሲያባንነን የሚያድረው ጉዳይ በሕልውናችን ላይ ያነጣጠረው የአንድነታችንና አብሮ የመኖራችን ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ አምና እንደገና በማገርሸት በአማራው ብሄር ላይ የተካሄደው ዘመቻ ኢትዮጵያዊነታችን ወይም ግዛታዊና ሕዝባዊ አንድነታችን እንዲሁም ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ የመኖር ባሕላችንን ጥያቄ ላይ የጣለ ዓመት ነበር፡፡ የአማራ ብሔር ተወላጆችን በማፈናቀል የተጀመረው ግፍ ዓመቱን በሙሉ በመስፋፋት የተለያዩ ክልሎችን አዳርሷል፡፡ ለዘመናት የዘለቀ አንድነታችንና አብሮነታችን ሳይሆን ለብሔር ልዩነቶቻችንና ለብዝሃነታችን ብቻ ልዩ ትኩረት የሚሰጥው የማንነት ፖለቲካ የሃገራችን አንድነትና አብሮ የመኖር ባሕላችንን ማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን አውሎ ማሳደር የማይችል ስር የሌለው ዘመን ያለፈበት ምልከታ መሆኑን ያስመሰከረ ዓመት ሆኖ ተጠናቋል፡፡

የዓለም ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከግል ማንነቱ ይልቅ አብሮነቱን በመሻት ከልዩነት ጎራ ወደ አንድነት ጎራ እየተሰባሰበ ባለበት በዚህ ክፍለ ዘመን ልዩነትን ለማስፍት ታቅዶ፤ በሕገ-መንግስት በተደነገገ የማንነት ፖለቲካ ቅርንጫፍ ላይ ተንጠልጥለን በጥርጣሬና በስጋት እየተያየን ሕይወታችንን እንደገፍ የተፈረደብን መሆኑን ተመክሮ እንድንወስድ

በተቀነባበረ መልኩ እንደ ኢትዮጵያዊ ስንገፋና ስንሰደድ ዓመቱን አገባደናል፡፡ ኢህአዴግ ዛሬም በዚሁ ስጋትና ጥርጣሬ ውስጥ እንድንዳክር ባደረገን የማንነት ፖለቲካው ውስጥ የራሱን ቤት ሰርቶ እራሱን አደላድሎ ሕይወቱን ቀጥሏል፡፡ እንደ ኢህአዴግ ፍላጎት ከሆነ ሁላችንም ከእለታት በአንዱ ቀን ከእንቅልፋችን ስንነቃ የትኛው ብሔር የመገንጠል ጥያቄ ይዞ ብቅ እንደሚል በማብሰልሰል ወይም ከአማራው ቀጥሎ የመፈናቀሉ እጣ ፈንታው የየትኛው ብሔር ይሆን በሚል ሰቀቀን ውስጥ እንደተጣድን እንድንዘልቅ ያደረገው እቅድ በከፊልም ቢሆን ይዞለት ዓመቱ ተገባዷል።

እንዳለፉት በርካታ አመታት ኢህአዴግ ለፖለቲካውና ፖለቲካውን ታከው ለመጡት ሹመኞቹ ቅድሚያ የሚሰጥ ድርጅት በመሆኑ በመልካም አስተዳደርና በፍትሕ ዙርያ ስር-ነቀል ለውጥ መምጣትም ሆነ ማሳየት አልቻለም። በሙስናና በግሽበት የተጠቃ ኢኮኖሚ የሚያደርስብንን ውጣ ውረድ ተቋቁመን ዕለት ጉርሳችንንና ኑሮአችን ለማሸነፍ የምናካሄደው ትንንቅ ተመልካች አጥቷል፡፡ ለዚህ ችግራችን መፍትሔው እንደሰማየ ሰማያት መራቁ ሳያንሰን በአናቱ ላይ መልካም አስተዳደርና የፍትሕ እጦት ያደረሰብንን መንገላታት እንደንለምደውና ለጊዜና ለሂደት እንድንተወው ስንመከር ከርመናል።

እንደተለመደው የዋጋ ግሽበት፣ የኑሮ ውድነት፣ ስራ አጥነትና ማህበራዊ ቀውሶች በቁጥጥር ስር እንደዋሉ ተደርጎ ድንቅ መዝሙር ቢዘመርላቸውም የፕሮፓጋንዳዎቹ ውርጅብኞች ከነባራዊ እውነታው ወጥተን የኑሮ ውጥንቅጣችንን እንድንዘነጋ በማድረግ የታቀደላቸውን አላማ አላሳኩም። በእርግጥ ዛሬም ቢሆን ሕይወታችንን በትናንት ስሌት ( ከደርግ ድከመት የተሻለበሚል ) ድፍንና ጥሬ ስሌት እየተለወሰ መራራውን ውሸት በግድ አምነንና ተቀብለን እንድንኖር ተፈርዶብናል፡፡ እንደተለመደው ስለዛሬ ለውጥና መሻሻል ስናወራ ትናንት ስለተፈጸመው ተዓምር ሲተረክልን ዓመቱ ተገባዷል፡፡ ያሳለፍነውን ለውጥ እንደወቅቱና እንደ አመጣጡ ተገልግለንበታልና ዛሬ ደግሞ ሌላ ቀን ስለሆነ ለዛሬ መልስ መሻታችን ግድ ቢሆንም በትናንት ሚዛን ሕይታችን እየተለካ ኑሮ እንደ ከበደን፣ መልካም አስተዳደርና ፍትሕ እንደናፈቀን፣ ሃሳባችንን በነጻነት የመግለጽ፣ የመወያየትና የመደራጀት፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረገና የመቃወም ሙብታችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ጥያቄ ላይ እንደወደቀ እንገኛለን።

ያለፈው አንድ ዓመት ጥቅል ጉዳዮች ለመንደርደርያነት ያነሳኃቸው ከዝርዝር ጉዳዮች በፊት አንባቢዎች ወደ ትክክለኛው መንፈስ እንዲገቡ ለማገዝ ነው፡፡ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ልግባ። ነጮች እንደሚሉት ሁሌም ፋይዳው( ሰይጣኑ) ያለው ከዝርዝሩ ውስጥ ነው።

ያለፈው ዓመት 2005 በራሱ ሲመዘን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ያልተጠበቁ ክስተቶችን ያስተናገደ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ዓመት ነው። ለዚህ የሚጠቀሱ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመርያው የዓመቱ ምዕራፍ የተከፈተው የኢህአዴግ አይዲኦሎግ (የሃሳብ አመንጭ) የነበሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊን እረፍትን ተከትሎ በኢህአዴግ ውስጥ የታየው የስልጣን ክፍፍልና ክፍተቱን ለመሙላት የተካሄደው ውጥንቅጥ ነበር።

ከጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ሞት በኃላ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ወጥ መስሎ ለመታየት ቢዋትትም፤ መደናበሩንና መርበትበቱን የሚያሳብቅበትን ፊቱን መደበቅ አልቻለም። መርበትበቱ የተጀመረው ገና ከጠዋቱ ላይ ነበር። ከእለተ እረፍታቸው ጀምሮ የኢህአዴግ ቱባ ባለስልጣናት ወደ መድረከ በወጡ ቁጥር የጠቅላይ ሚኒስቴርነት አሿሿም አስመልክቶ ሕገ መንግስቱ ላይ የሰፈሩት አንቀጾች ምን እንደሚደነግጉ እንኳን በቅጡ የማስረዳትም ሆነ የመተርጎም አቅም አልነበራቸውም። በነጋታው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቦታ ወድያው( አውቶማቲካሊ) በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እንደሚተካ በፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች የተሰጠውን ማብራርያ ውሎ ሳያድር ከገለልተኛ የሕግ ባለሙያዎች የሰጡት ትንታኔና የሕዝቡ ዋይታ መበራከት በድርጅቱ ውስጥ መደናገር ስሜት በመፍጠሩና በተለይ ደግሞ የብሄር መስመርን ተከትሎ ስልጣኑ ይገባናል የሚል ጥያቄ ያላቸው ሃይሎች በፓርቲው ውስጥ ከፍተኛ ጉርምርምታ በመቀስቀሳቸው፤ ወይ ለማሳመን ወይ ለማስገደድ የኢህአዴግ አመራር የረሳውን ሕገ-መንግስት ወደ መበርበር እንዲገባ ተገዶ ነበር።

በእርግጥም ኢህአዴግ ከጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ውጭ ሁሉ ነገር ጨለማ የሆነበት ድርጅት እንደሆነ በገሃድ ያሳየ አስገራሚ ክስተት ነበር። በአገኙት አጋጣሚ ሁላ ድርጅታቸው በርካታ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ለዚህ እንደበቃ ደም ስራቸው እየተገታተረ የሚሚገቱ የኢህአዴግ አባላት ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስን ሲያጡ የተፈጠረባቸው ትርምስ መቋጫ ጠፍቶት ለወራት እንደዘለቀ ቀጥሏል፡፡ ኢህአዴግ በዋነኛነት እራሱ የቀረጸውን ሕገ-መንግስት ለማብራራትና ለማስርዳት የባጥ የቆጡን በመባጠጥ ሲዋትት ማየት የኢህአዴግን አንጋፋነት ጥያቄ ላይ የጣለ ፈታኝ ዓመት ነበር።

ከሙስሊሙ ማህበረሰብ የወጡ ሃይሎች ያነሱትን የሙብት ጥያቄ በውክልና ሲመሩ የነበሩ ግለሰቦች መታሰርን ተከትሎ የሙብት ጥያቄውና እንቅስቃሴው ሰፋትና ጥልት ያገኘበት ዓመት ነበር፡፡ ጥያቄው ከተወሰኑ መስኪዶችና ከአዲስ አበባ ወጥቶ ወደ ተለያዩ የሃገሪቱ ከተሞች ከመስፍፍቱም በላይ ጉዳዩ ኢህአዴግ እንደሚለው የጥቂት ሙስሊሞች ጉዳይ ብቻ አለመሆኑን ያሳየ ነበር፡፡ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በመውጣጣት የተቋቋመው ኮሚቴ እንቅስቃሴውን የመራበትና ያስተባበረበት መንገድ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ አልፎ የበርካታ ሰዎችን ቀልብ የሳበ ነበር፡፡ በተለይም በዓመቱ ማገባደጅ ላይ የሰማያዊ ፓርቲ የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ በስፋት በመቀላቀል ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግሉ የተለየ ድምቀት ሰጥተውት ነበር፡፡ በስተመጨረሻ ከመንግስት በኩል በተወሰደው ሃይል የተቀላቀለበትና ማስፈራሪያ የታከለበት እርምጃ እንቅስቃሴው የተገታ ቢመስልም መንስኤው ምንም ይሁን ምን የሙብት ጥያቄው ያዘገየው ይሆናል እንጂ መንግስት በተከተለው መንገድ ሊፈታም ሆነ ሊገታ እንደማይችል ሂደቱ በቂ ተመክሮ የሰጠ ነበር፡፡

ኢህአዴግ እንደተለመደው የሕዝብ ዝምታና ቸልተኝነት እንደ ይሁንታ በመውሰድና እዚህም እዚያም የታቀዱ ጅምር የልማት ስራዎች በመንተራስ ፈርጀ ብዙ የሆኑትን ኢኮኖሚያዊና ዴሞክራሲ ጥያቄዎች ለማዳፈን በፕሮፓጋንዳነት ለመጠቀም ከሚዳከረው አስተሳሰቡ መላቀቅ አልቻለም፡፡ ኢህአዴግ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ወቅታዊ አጀንዳዎች በማዘናጊያነት መጠቀሙን ትቶ ለሕዝብ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጥያቄ ተጨባጭ፣ ፈጣንና እርኪ መልስ መስጠት ካልጀመረ ደርግን የጣለው ኢትዮጵያዊያ ቸልተኛነትና ንቀት ኢህአዴግንም ግብአተ መሬቱን ማፋጠኑ የማይቀርለት አደጋ መሆኑ ያመላከተ ዓመትም ነበር፡፡

ደርግ ከኢህአዴግ የተሰነዘረበት የጦርነት በትር እንዲበረታበትና ግብአተ መሬቱ እንዲፋጠን መንስኤ ከነበሩት ጉዳዮች መካከል አንዱ በፕሮፓጋናዳው ውርጅብኝ የተሰላቸው ኢትዮጵያዊ ለደርግ ልፈፋ ጀሮ መስጠት ማቆመ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በእርግጥም በተጽእኖና በማስፈራራት "አብዮት አደባባይን" እያጥለቀለቀ ግራ እጁ እስኪዝል ቢወረውርም የሕዝብ ልቡ ከሸፈተ ውሎ ያደረ በመሆኑ ቁጣውን በተናጠል ለመግለጽ ሰላማዊ ሰልፉ እስኪበተን ድረስ የሚዘገይ አልነበረም፡፡ ልቡ ቢሸፍትም ተሰለፍ ሲባል በነቂስ ወጥቶ ይሰለፍ የነበረው ሕዝብ ለእናት ሃገር ጥሪ አዋጣና ዝመት ሲባልም እምቢተኛ አልነበረም፡፡ እውነተኛ ስሜቱ ይገለጥ የነበረው ግን ከሰልፍ ሲመለስ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ለደርግ ባለመተባባርና ለፕሮፓጋንዳው ጆሮ በመነሳት ጥላቻውን በመግለጥ ነበር፡፡ በመጨረሻ ላይም ከጦር ሜዳ ጥሎ በመጥፋትና እጁን ለኢህአዴግ በሺዎች በመስጠት በእምቢኛነት፣ በቸልተኛነትና ባለመተባበር ደርግን አዳክሞ ለሽንፈት ዳርጎታል፡፡

በደርግ ዘመን የጓድ መንግስቱ ሃይለማርያም ፕሮፓጋንዳ ቋቅ እስኪለን ድረስ ከመሰልቸታችን በላይ ማብቂያ ላልነበረውና ለከንቱ ጦርነታቸው ማገዶ አንሆንም በማለታችን ደርጎችና መሪያቸው ሕዝብን እስከመሳደብና ማዋረድ ደርሰው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ደርግ በወቅቱ የሕዝብ ጥያቄን መመለስ እንዳቃተው ልቡ ቢያውቅም፤ በስልጣን ላይ ለመቆየት ከነበረው ከፍተኛ ልክፍት የተነሳ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨት፣ አንዱን ብሔር በሌላው ላይ ወይም አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ በማነሳሳት ከፋፍሎ ለመግዛት የአቅሙን ተወራጭቷል፡፡ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም የሚቻለውን ሁላ ሞክሯል፡፡ ከድሕነት መላቀቂያው እውነተኛ ቀን የራቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደርግን እግር እሳት ሆኖ ለመፍጀት የግብጽ አብዮት አላስፈለገውም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢህአዴግን ለመቅጣት ዛሬም የግብጽ ዓይነት አብዮት ያስፈልገዋል ብዬ አላምንም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነኖችን የሚታገልበት ከግብጽና ከቱኒዚያውያን በእጅጉ የተለየ የራሱን የሆነ የተለየ መንገድ አለው፡፡ ድሕነት፣ አምባገነንነት፣ መልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ እጦት ሲያንገፈግፉት የሃሩን ሕልውና አስጠብቆ በአምባገነኖች ላለመገዛትም ሆነ ላለመተዳደር ባለመመቸት፣ ገዢዎቹ መሬት የማትመቻቸው ገሃነም ማድረግን እንደሚችልበት ደጋግሞ አስመስክሯል፡፡

የዜጎችን ሕይወት ማሻሻልም ሆነ መሰረታዊ ችግራቸውን መቅረፍ ያቃተው የደርግ ሶሻሊዝም በይዘቱ ይለያይ እንጂ እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሁላ የአረንጓዴም ሆነ ኢንዱስትሪ ልማት እቅድ ነበረው፡፡ ደርግ በሲሚንቶ፣ በጨርቃ ጨርቅና በቢራ ፋብሪካዎች ልማቱን ሞካክሮት እንደነበረም የሚረሳ አይደለም፡፡ ከወቅታዊ አጀንዳና ሽር ጉድ ያልዘለለና ውስጡ ሙስናና ግሸበት እንደ ብል የሚበሉት ልማት የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሆኖ ማገልገል የሚችለው በወቅታዊ መሳሪያት ብቻ ነው፡፡ ውሎ አድሮ ግን ምኞቱንስ ጠገብን "ዳቦው የታለ" የሚል ጥያቄ ማስከተሉ ከወዲሁ ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ጥያቄው ገዝፎና አፍጥጦ ሲመጣም እንደተለመደው "ቆይ ነገ" መልስ ሆኖ ሊያውል ሊያድር አይችልም፡፡ ለዘንተዓለም "ቆይ ነገ" ተስፋ ሆኖ ሊቀጥል እንደማይችል ኢህአዴግ ከደርግ ሊማር ይገባል፡፡

ደርግ በወቅቱ ያስብ እንደነበረው ዛሬ ላይ ኢህአዴግ የሕዝብ ዝምታንና ቻልተኝነትን ሽንፈት አድርጎ መውሰዱ ከባድ ስህተትና የዋህነት ነው፡፡ የግብጽና የቱኒዚያ አብዮት ወደ ኢትዮጵያ አለመዛመቱ ለኢህአዴግ ከሕዝብ በስልጣኑ ላይ እንዲቆይ እንደተቸረው ይሁንታ ተወስዶ ፕሮፓግንዳ ሲሰራበት መመልከታችን የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የግብጽን ወይም የቱኒዚያን ሕዝብ ባለመሆኑ የታህሪሪ ቁጣ ወይም የቦአዚዝ አብዮት አያስፈልገውም፡፡ ኢህአዴግ የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ዴሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብት ጥያቄ በቁርጠኝነትና በአጭር ጊዜ መፍታት ካልቻለ ደርግን የጣለው ሕዝባዊ ቻልተኝትና እውቅና መንሳት ኢህአዴግንም ማስወገዱ አይቀሬ ነው፡፡ የተራበ፣ የተጠማ፣ መሰረታዊ ፍላጎቱ ያልተሟላ ሕዝብን በፕሮፓጋናዳና በአንድ ለአምስት ጠርንፎ መጓዝ ለብዙ ዘመን ሊቀጥል አይችልም፡፡

ኢህአዴግ ባለፈው ዓመት "መለሳለስ" ካሳየባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ለሰላማዊ ሰልፍ ያለው ዝንባሌ መሻሻሉ ነው፡፡ የሰማያዊ ፓርቲ ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት የራሱን ተጽእኖ መፍጠሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኃላ ውስጥ ለውስጥ በወጣ መመርያ ታግዶ የነበረው ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ መብት የኢህአዴግን ይሁንታ አግኝቶ እንደገና ነፍስ ዘርቷል ፡፡

የሚበረታታ መልካም ጅማሮ ነው፡፡ ይህም ሆኖ የኢህአዴግ ፍላጎት ምን እንደነበረ መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ኢህአዴግ ሰላማዊ ሰልፍ ሲፈቅድ ከልቡ ለሕገ-መንግስታዊ መብታችን ከመቆርቆር እንዳልነበር አመላካች ጉዳዮች አሉ፡፡ በእርግጥም ኢህአዴግ እንደ ስልት የተከተለው ሰላማዊ ሰልፉን ስፈቅድ በአንድ በኩል የዓለም አቀፍ ማህበረሰብን ይሁንታ አገኝበታለሁ ከሚል ስሌትና በሌላ በኩል ሰላማዊ ሰልፉ የሚያደርገው ድርጅት ስለማይሳካለት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊ የላቸውም ብዬ ለማሳጣት ይጠቅመኛል ከሚል ሴራ የመነጨ ነበር፡፡ ሰላማዊ ሰልፉንና ተቃዋሚውን አሳንሶ ለማሳየት የነበረው ጥረት መገለጫ ነበር፡፡

ሕዝቡን በምፈልገው መጠን አሸማቅቄዋለሁ፡፡ ጥቂቱ ደግሞ በጥቅም ይዢያለሁ፡፡ ቀሪውን በአንድ ለአምስት ጠርንፌያለሁ፡፡ በዚህ መንገድ ሕዝቡ ምን እንደሚያስብና ምን ሊያደርግ እንደሚችል በቂ መረጃ አለኝ ከሚል ግብዝ መንፈስ በመነሳት በሰላማዊ ሰልፉ ላይ አንድም ሰው ዝር አይልም የሚል መላምት በኢህአዴግ በኩል ተወስዶ እንደነበረ ሂደቱ ይገልጻል፡፡ ለዚህ ደግሞ አይነተኛ መገለጫው ኢህአዴግና የፕሮፓጋናዳ ማሽኖቹ ትኩረት የሰጡት ሰላማ ሰልፍ የማድረግ ሙብት ስለመከበር ሳይሆን ሰልፉ ላይ ስለወጣው ሰልፈኛ ቁጥሩ የነበራቸው እሰጣ አገባ ነው፡፡ ይህም ሆኖ አጋጣሚው ግን ኢህአዴግ የጠበቀው አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድ ለአምስት ጥርነፋውን ሰብሮ በመውጣት በሰላማዊ ሰልፉ ላይ በነቂስ በመገኘት ጥያቄውን አሰምቷል፡፡ ልቡ ለኢህአዴግ ፕሮፓጋናዳ ምርኮ እንዳላሆነና ለጥርነፋው እጅ እንዳላሰጠ በማያሻማ መንገድ ማሳየት ችሏል፡፡ በተለይ የሙስሊሙ ማህበረሰብንገና ከጅምሩ ሰልፉን በማድመቅ ና የሃይማኖት ልዩነቱን በመስበር ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል፡፡

ባለፈው አመት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ሌላው ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ ነበር፡፡ የ2005 አዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይተወቅና ለግምት በሚያዳገት ደረጃ ዴሞክራሲያዊነቱ በእጅጉ የወረደ ነበር፡፡ ምርጫ የሚያሰኝ አንዳችም መስፈርት ያልነበረውና ኢህአዴግ ብቻውን ተወዳድሮ ብቻውን ያሸነፈበት ሂደት ነበር፡፡ አማራጭ ስላልቀረበበትም ምርጫው በእርግጥም የሃገር ሃብት በከንቱ የፈሰሰበት ምርጫ ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ ኢህአዴግ ከጅምሩ በስጋትና በጥርጣሬ ድባብ ውስጥ ሆኖ በር ለበር አስገዳጅ ቅስቀሳ ከማድረጉም በላይ ለምርጫ ያልተመዘገቡ ሰዎችን ስም ዝርዝር ከቀበሌ ነዋሪዎች መዝገብ ላይ በመገልበጥ ማስፈራራትና ተጽእኖ የታከለበት የመራጮች ምዝገባ እንዲካሄድ አደርጓል፡፡ የነዋሪነት መታወቂያ ሳይጠየቅ ምርጫ ካርድ ታድሏል፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተገቢውን የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ድጋፍ የከለከለ ከመሆኑም በላይ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

የምርጫው ዕለት ተወዳዳሪ ባይቀርብበትም የምርጫው ሂደትና ወጤት ያለውና "ቅቡል" ለማስመሰል መራጩን ሕዝብ አስገድዶ ወደ ምርጫ ጣቢያ ለመንዳት ኢህአዴግ ያደረገው ሙከራ በመራጩ እምቢተኝነት ከሽፏል፡፡ የምርጫው ሂደትም ሆነ ውጤት ከኢህአዴግ በስተቀር የማንንም ይሁንታ ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ ከዚህ የምርጫ ሂደት ጅምር የምርጫ

ስርዓታችንና ዴሞክራሲያችን የተጋረጠበት አደጋን ኢህአዴግ ልቦና ካለው ሊማርበት የሚገባ ትልቅ ትምህርት ሰጭ እድል ሆኖ አልፏል እምነት አለኝ፡፡

በመጨረሻ ላይ ማንሳት የምፈልገው ጉዳይ ከአጀንዳዎቼ ሁሉ ያለፈውን ዓመት በሃዘኔታ እንዳስብ ያደረገኝ፤ የአማራ ብሔር ተወላጆች ከሶማሊያ፣ ከደቡብና ከቤንሻንጉል ክልል የመፈናቀላቸው ጉዳይ ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ ላይ ዜጎች በማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል ተዘዋውረው መስራት እንደሚችሉና እንቅስቃሴያቸው እንዳይገታና በማንነታቸው በደል እንዳይደርስባቸው ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ቢደነግግም በርካታ ቁጥር ያላቸው የአማራ ብሔር ተወላጆ ከተለያዩ ክልሎች ያፈሩትን ሃብትና ንብረት ለመሰብሰብ እንኳን እድል ሳያገኙ ለእንግልትና መፈናቀል ተዳርገዋል፡፡ መፈናቀል ብቻ አይደለም ለበርካታ አደጋ፣ ለወረርሽኝ በሽታ ለጤና እክል አልፎ ተርፎም ለሞት ተዳርገዋል፡፡

ማንም የሰው ፍጡር አሜሪካ መሬት ላይ መወለዱ ብቻ ከነ ሙሉ መብቱ አሜሪካዊ ያደርገዋል፡፡ አሜሪካ ውስጥ በገደብ ለተቀመጠ ጊዜ መኖር የቻለ ሰው ከነሙሉ ጥቅሙና ግዴታው አሜሪካዊ ለመሆን ይችላል፡፡ ኢትየጵያዊ ሆኖ፣ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ተወልዶ ያደገ ኢትዮጵያዊ፤ ኢትዮጵያዊ መሆን አለመቻሉ ወይም እንደ ኢትዮጵያዊ አለመቆጠሩ ከአፓርታይድም የባሰ አስከፊ ዘረኝነት ከመባለት ውጭ ሌላ ትርጉም ልሰጠው ያዳግተኛል፡፡ የሰው ፍጡር ባድመን ለማስመለስ ሕይወትን ያህል ክቡር ዋጋ ከመክፈልና አካልንና ደምን ከመገበር በላይ የኢትዮጵያን መሬት አርሶ ሕይወትን ለማቆየት ምን ዓይነት ግብር መክፈል ይቻላል፡፡

የትኛው ኢትየጵያዊ ይሆን ከሚያርሰው እፍኝ አፈር ተቆንጥሮ በመሰራቱ በመሬት ላይ ብቸኛ ባለመብት ሊሆን የሚችል? በዚህስ ምክንያት የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው የኢትዮጵያዊ ወንድሞቹን ሃብትና ንብረት ነጥቆ ከቀያቸው የመንቀል ምድራዊ ስልጣን የተሰጠው፡፡ ከቅድም ተከተል በስተቀርስ መሬትን የፈጠረና ጠፍጥፎ የሰራ ያ ኢትዮጵያዊ የቱ ነው? ሃገርን ጠብቆ ማቆየት ለዚህ ስልጣን የማያበቃ ከሆነ አስካሁን ድረስ መስዋእትነት ከከፈለው ኢትዮጵያን አስከብሮ በማቆየት የወላይታ ደም ከኦሮሞው ወይም የአማራዊ ደም ከትግሬው ደም እንዴት የተሻለ ሊሆን ይችላል? ከሕንድን ከቻይና በልማት ስም ዜጎቻቸውን ለመቀለብ በርካታ መጤዎች በብሔር ብሔረሰቦች መሬት ላይ ዜጎቻችንን አፈናቅለው መስፈራቸውን የተቀበለ፣ መንገዱን ያመቻቸና ጥርጊያ መንገድ የዘረጋ ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ መሬት ላይ ሰፍረው፤ ሌላ ሳይሆን ሕይወታቸውን ለማቆየት መቻላቸውን እንደ ሃጢያት መቁጠሩ "ድንቄም የብሔር ብሔረሰብ ፍቅር" የሚሰኝ ትዝታ ጥሎ ያለፈ ዓመት ነበር፡፡

ብሔረተኝነት በመቻቻል፣ እውቅና በመሰጣጠት የጋራ ተጠቃሚነት ካላረጋገጠ መዘዙ ብዙ ነው፡፡ በቅጡ ያልተያዘና የከረረ ብሔረተኝነት ለፋሺዝም፣ ለዘረኝነትና ለሰው ልጅ ጥላቻ አሳልፎ እንደሚሰጥ ዓለማችን በቂ ምስክር አላት፡፡ የብሔር ብሔረሰቦች የቡድን መብት መከበሩ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል የሰው ፍጡር በብሔር ማንነቱ ሳይሆን በግለሰብነቱና በሰውነቱ ብቻ የመኖር መብቱ ሊከበር እንደሚገባ ጥያቄ ማስነሳቱ ውሎ አድር አደጋውና መዘዙ ብዙ ነው፡፡

ብዝሃነታችን የመቻቻል የመከባበርና የአንድነታችን መገለጫ ሊሆን እንጂ ከመቃብር ማዶ ባሻገር ሄደን ልዩነቶቻችንን ፈልፍለን በማውጣት የግል ተጠቃሚነታችንን የምናራምድበት ቂምና ቁረሾ አርግዘን በቀል የምንወጣበት ሊሆን አይገባም፡፡ ሃገራችንና ሕዝባችንን ከዚህ ዓይነት ፈተና ለመታደግ መጭው አዲስ ዓመት በልቦናችን እንዲያሳድርልን አዕምሮአችንን ክፍት እናድርግ፡፡

መልካም አዲስ ዓመት ! !